የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
የዋሽንግተን ዲሲ እና አካባቢው
ሀገረ ስብከት ጽሕፈት ቤት

**The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church**
**Archdiocese of Washington DC**
**and its surroundings.**

መስከረም ፩ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ

አሜን

“ወትባርክ  አክሊለ ዓመተ  ምሕረትከ”

በቸርነትህ ዓመትን ታቀዳጃለህ፡፡ መዝ ፷፬፡፲፩።

የተከበራችሁ አባቶቼና እናቶቼ ወንድሞቼና እኅቶቼ በሀገራችን በኢትዮጵያና በአለንበት አገር በሰሜን አሜሪካ እንዲሁም በዓለም ዙሪያ ለምትገኙ በሙሉ፤ ከሁሉ አስቀድሞ የዘመናት ባለቤት ከዘመናት በፊት የነበረ ዘመናትን አሳልፎ የሚኖር አምላከ አማልክት እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁንና እንኳን ከዘመነ ሉቃስ ወደ ዘመነ ዮሐንስ በሰላምና በጤና አሸጋገራችሁ አደረሳችሁ።

አዲሱ ዘመን ማለት ዘመነ ዮሐንስ የምግባር የሃይማኖት የሕይወት የጤና የእውቀት  የብልጽግና ዘመን እንዲሆንላችሁ በዲሲና አካባቢው ሀገረ ስብከት ስም መልካም ምኞቴን ስገልጽ ከመንፈሳዊ ሰላምታ ጋር ነው።

ቅዱስ ዳዊት “በቸርነትህ ዓመትን ታቀዳጃለህ” በማለት የእግዚአብሔርን ቸርነት መሐሪነት ይቅርባይነት አጉልቶ ያሳያል። ለፈጣሪውና ለፍጥረታት መጋቢ  የሚገባውንም ምስጋና ያቀርባል። ምክንያቱም ቅዱስ ዳዊት ሰው በዚህ ዓለም የሚሠራውን ግፍ በቀጥታም በተዛዋሪም ጠንቅቆ ያውቃልና። ስለዚህም ከተወሰኑ የእግዚአብሔር ወዳጆች በቀር እንደ ዓለም ወዳጆች አስአተሳሰብና ኑሮ ዓመትን መቀዳጀት አይደለም ደቂቃዎችን እንኳ መቀዳጀት የማይታሰብ ነው። በዘመናችን እንደሚታየው ሁሉም አስተካክሎ የበደለበት ዘመን ነው። እግዚአብሔር ለሁሉም የሰው ልጅ  እንደየሥራው የዘመን  ዋጋ እንዲከፈለው ቢወስን ኖሮ ዓለም ከሰው ልጅ መኖርያነቷ ይልቅ የአራዊት መፈንጫና መናህሪያ መሆኗ አነጋጋሪ አይሆንም። በየጊዜው ከምንሰማውና ከምናየው አንጻር እገሌ መንፈሳዊ ነዉ እገሌ ሥጋዊ ነዉ ለማለት እንኳ አያስደፍርም። በሙሴ ዘመን በምድረ በዳው ጉዞ እንደሆነው ዛሬ በዓለም ዙሪያ በሃይማኖት ሰዎችም  ይሁን በዓለም ሰዎች የምግባር ስድነቱ በዝቷል።

“ሙሴም በጠላቶቻቸው ፊት እንዲነወሩ አሮን ስድ ለቋቸዋልና ሕዝቡ ስድ እንደተለቀቁ ባየ ጊዜ በሰፈሩ ደጅ ቆሞ የእግዚአብሔር ወገን የሆነ ወደኔ ይምጣ” አለ፡፡ ዘጸአት ፴፪፡ ፳፮። ከዚህም ቃል እንደምንገነዘበው ትናትም ሆነ ዛሬ ለምእመናን ጥፋትና ውድቀት አስተዋጽኦ ያደረግነው በእግዚአብሔር ቤት የተቀመጥነው መንፈሳዉያን መሪዎች፤ ከስም ያላለፈ ሥራ ባለመሥራታችን ነው። እንደ ነቢዩ ሙሴ የእግዚአብሔርን ወገን ለይተን በእግዚአብሔር ቤት እንዲኖር ወደ እግዚአብሔር ቤት ከመጥራት ይልቅ፤ የውስጡን ገፍቶ ማስወጣትና ማሳደድ የውጩን አመሳስሎ ማስገባት የየዕለት ተግባራችን ሆኖአል። ከዚህም የተነሳ የምንሰማውን የዋይታ ወይም የደስታ ድምጽ መለየት ተስኖናል።

ስልክ/**Telephone: 703-360-0105**    **www.eotcdc.org**    **Email: office@eotcdc.org**
አድራሻ/**Address: 4210 Corcoran St. Alexandria, VA 22309** ወይም/**or P.O. Box 77363 Washington, DC  20013-7363**

"ኢያሱም እልል ሲሉ የሕዝቡን ድምፅ ሰምቶ ሙሴን የሰልፍ ድምፅ በሰፈሩ ውስጥ አለ አለው እርሱም ይህ የድል ነሺዎች ወይም የድል ተነሺዎች ድምፅ አይደለም ነገር ግን የዘፈን ድምፅ እሰማለሁ" አለ። ዘጸአት ፴፪፡፲፯። አዎ የእግዚአብሔር ሰዎች የእግዚአብሔርን ወገኖች ድምፅ ይሰማሉ። መዝሙርን ከዘፈን፤ ዋይታን ከዕልልታ፤ እዉነትን ከሀሰት፤ መምሰልን ከመሆን፤ ለይተው ያውቃሉ። ራሳቸዉን ለ እግዚአብሔር ከሰጡት በቀር ብዙዎች የእግዚአብሔርን ቤት ከግለሰብ ቤት መለየት ተቸግረዋል። የዕለቱን እንጂ ያመቱን ማሰብ አቁመዋል። ቁሳቁስን እና ሥልጣንን እንጂ እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ ዘንግተዋል። "የሰዉ ሁሉ ዐይን አንተን ተስፋ ያደርጋል። ምግባቸውንም በየጊዜው ትሰጣቸዋለህ"። መዝ፻፵፬፡፲፭።

እግዚአብሔርን የሚያምን ተስፋው እግዚአብሔር ነው። ዐይኖቹንም የሚያነሳ እጆቹን የሚዘረጋ ወደ እግዚአብሔር ነው። እሱም እንደ ሥራው ሳይሆን እንደ ቸርነቱ፤ ለስጦታው ንፍገት ጉድለት የሌለበት እግዚአብሔር እንደሚያደርግለት ያምናል። በተሳሳተና በረከትን በሚያሳጣ መንገድ ለሚገኝ ሥልጣን ጥቅም ወዘተርፈ እጁን አይሰጥም። ዔሳዉና ያዕቆብ ለዚህ ምሳሌዎቻችን ናቸው። ዔሳው ተስፋውም አመለካከቱም ምድራዊ ሆነ፤ የቸርነቱን ስጦታ ረሳ ብኩርናውን በጥቅም ለወጠ። ያዕቆብ ግን የሚያደርገውን የሚያውቅና ተስፋው እግዚአብሔር ስለሆነ በተዛዋሪ መልኩ በረከትን እንዲቀበል እናቱ ርብቃ ስትመክረው እንዲህ ነበር ያላት።

"ምናልባት አባቴ ቢዳስሠኝ በፊቱ እንደሚዘብት እሆናለሁ መርገምንም በላዬ አመጣለሁ በረከትን አይደለም"። ዘፍ ፳፯፡፲፪።

ወገኖቼ ከዚህ ቃል ብዙ መማር ይቻላል። ኃጢያት ምንጊዜም ኃጢያት ሲሆን ራስን የሚጎዳ ኃጢያትና ሌዉን የሚጎዳ ኃጢያት ልዩነት አለው። በዘመናችን እየታየ ያለው ኃጢያት ትውልድን፤ሀገርን፤ከመጉዳቱም በላይ የእግዚአብሔርን ቸርነት የሚፈታተን ነው። እግዚአብሔር ከቸርነቱ ብዛት የተነሳ በሰጠን ዘመን ላይ ተቀምጦ፤ ህሊናን ሸጦ ዐይንን ጨፍኖ በማን አለብኝ ባይነትና በግድ የለሺነት፤ ሥጋዊ ምኞትንና ፍላጎትን ለማሟላት ሲባል ብቻ በየዘመኑ የተነሱ አባቶቻችን ለሃማኖት ለታሪክ፤ለነገ ለትውልድ፤ በሚል የደከሙበትን ሁሉ ወደጎን በመተው፤ ለሰውም ሆነ ለእግዚአብሔር የማይመች ሥራ መሥራት በሰው ፊት አደለም በእግዚአብሔር ፊት እንደመዘበት ነው። ያዋቂ አጥፊ መሆን በራሱ በረከትን ያሳጣል መርገምንም ያመጣል። ስለሆነም የዓመታቱ መለዋወጥ ወይም መቀያየር ከኛ ሕይወት ጋር ዝምድና ሊኖረው ይገባል። ሕይወታችን ከከፉ ምኞቱና ፍላጎቱ ተለውጦ በሃይማኖትና በምግባር፤ በአንድነትና በሕብረት፤በመግባባትና በፍቅር፤ በተሰጠን የዘመን መክሊት ለሀገር ለወገን ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልናስብና የየድርሻችንን ለመሥራት ትንሳኤ ልቡና ሊኖረን ግድ ይላል። ከዚህ ውጭ ዘመን ማስቆጠሩ "ተኖረና ተሞተ" የሚለውን የምፀት ቃል ያስጠቅሳል። ስለሁሉም ነገር አምላካችን እግዚአብሔር በበደላችን ምክንያት የቸርነቱን በር ሳይዘጋ ከዘመነ ሉቃስ ወደ ዘመነ ዮሐንስ ስለአሸጋገረን ክብርና ምስጋና ለርሱ ይሁን ።ምንጊዜም የቸርነቱን አመት እሱን ደስ በምናሰኝበት መልኩ ያቀዳጀን።

አምላካችን እግዚአብሔር ለሀገራችን ለኢትዮጵያና ለዓለም ሁሉ ሰላምን ይስጥ

ይችን የምንኖርባትንም ሀገር ምድረ አሜሪካን በረድኤት ይጠብቅልን።

አባ አብርሃም የዲሲና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ